2) Baaluk caddo maadewee awki biyaakitah yan waqdi biyaakak uruh faxximma intam aba.

180. Baaluk caddo maadewee awkih maynub

Qaaqise baaluk caddo maadewee awka meqennal qarsa/yaynabe.

181. Baaluk caddo maadewee awkak ayyuntiinoh angaaraw

1) Qaaqise baaluk caddo maadewee awkak ayyuntiinoh angaaraw miraacisaah lowsiisah.

2) Takkay immay qaaqise dudda le sabab allekalah baaluk caddo maadewee awka iroh loowimta xaltani lih angoorowe kaa kalam maxiqa.

182. Amôladih barittoo kee mihratiini aydakaakan akah geyannih dirki

Qaaqise baaluk caddo maadeweeh yan awkih karmaa kee xiqto lih qeedal leh tan amôladih wonna hinnay mihratiini aydakaakan akah geyannah abaanam faxximta.

183. Baaluk caddo maadeweeh yan awkih culenta

1) Qaaqise baaluk caddo maadeweeh yan awkih

179.አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ጤና አጠባበቅ

1) አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የጤንነት ሁኔታ ይከታተላል
2) አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሲታመም ከህመሙ እንዲፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወሰዳል ።

180.አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግ

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ መልካም አስተዳደግ ይመራል ።

181.አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት

1) አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል ይቆጣጠራል ።
2) ሆኖም አሳዳሪው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም።

182.አጠቃላይ ትምህርት እና የሙያ ስልጠና እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ

አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ እድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

183.አካለ መጠን ያልድረሰው ልጅ ገቢ

1) አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅዬው ጥቅም ያውላል።
2) አሳዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም።

culentitte hirigak awki tuxxiiqil asisa.

2) Qaaqise maalu macah ayfaafayal asisem baxxaqisaamih dirki kaal matan.

184. Fayya le culenta

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkih culenti fayya yeellek qaaqise awkak Abba wonna hinnay Ina akkeweek cokmí buxa ta madqak maasayyak 183 (2) madqimtem abbinoowe akah waytannah soolisam xiqah.

2) Cokmí buxah amri yantacawwe waqdi baaluk caddo maadewee awkih maynub kee barittoh kaa xiqah akak iyyan maali caddibnaa kee edde mekkeltimta uddur argaquk qaaqisel akah yaceen innah abta.

3) Raqeh yan maalu boqoysirat taamal asisuh quukah yan numih gabal daffessa.

185. Baaluk caddo maadeweeh yan awki taamak geyah yan culenta

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkih karma 14 sanatak bisoh gacta waqdi taamak geyah yan culenta sinnih hirga.

2) Isi makmok maaqabo takkem qaaqisel yeceek gamadal raqte lakqo ta madqal kaah yeceenih yanin qaaqak ugutak edde xoqoysimaamah currik yan.

186. Acwa wonna hinnay nagrah tabte gadditte wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awki acwah wonna hinnay nagrah gadda kaah cabah yan

184.ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ

1) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት በዚህ ህግ አንቀጽ 183(2) የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል ።

2) ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን የሚሰጥበት ጊዜ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ አስተዳደግና ለትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪ እንዲሰጠው ያደርጋል ።

3) ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ስራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ያደርጋል ።

185.አካለመጠን ያለደረሰው ልጅ ከስራው ስለሚያገኘው ገቢ

1) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እድሜ ከ14 ዓመት በላይ ሲሆን ከስራው የሚያገኘውን ገቢ እራሱ ይቀበላል።

2) ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪ ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነጻነት አለው ።

186.በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች

1) አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው ሊያዝ ይችላል።

2) በስጦታ ውል ወይም በኑዛዜው ስለንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘው ገቢ የተመለከቱ ሀይለ

num awki qunxam fanah qaaqise kaah hirigak tuxxiiqil asisuh amrisam xiqah.

2) Acwah ambalal wonna hinnay rabtô farrimtul ikoytá xiinissoo kee geytimah yan culenta wagittaamal madqimtem abbinowtam faxximta.

187. Meklah uddur akak maadewee culentitte

Meklah uddur akak gufewee culentitte qaaqise dirkih edde culam maxiqa.

188. Xaltanî qaaqa wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkak inaa kee abba qaaqiseynit takke uddur xiinissoh abtoota agaarad kee sittingeyil aban.

2) Inaa kee Abba sittinway sinnih dubuk wonna hinnay idoolinnal yafrigeenim xiqeween kaa tekkek ken nammayak numukteeni xayyoysah yan malkitik ugutak cokmí buxa baaluk caddo maadeweeh yan awkah aakam acayuk cokmi abta.

3) Ta maasayyak lani maasayyak (2) madqimtem elle tan innal elle anuk inaa kee abba qaaqisiyyal yaceen margaqal malkit keenik xayyowtam maxiqta.

189. Xaltanî baxsimiyya

Xaltani baxsimteemih sabbatah qaaqisiyyi reeda inki xaltanil dubuk radda waqdi ta xaltani taceeh tan margaqal qaaqisaanamih abtol anewaah yan dagaraay, iroh loowimtah tan xaltaniiy, wonna hinnay baaluk caddo maaddeh tan toobokoo kee maqanxiixik numuk teeni malkit cokmí buxal xayyoysam xiqah.

ቃሎች ተፈጻሚ መሆን አለባቸው።

187.የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች

የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም ።

188.ስለ ወላጆች ስልጣን

1) **አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ ።**
2) **አባት እና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሳኔ ይሰጣል ።**
3) **በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም ።**

189.የወላጆች መለያየት

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱ ስልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ፣ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን፣ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች፣ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ ።

190.አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ

190. Qaaqise baaluk caddo maadeweeh yan awkak xaltani akkewaa uddur

Qaaqise baaluk caddo maadeweeh yan awkak xaltani akkewaa kaa tekkek awka yaynabeenim wagittaamal tantacawweh tan margaqal xaltanik numukteeni wonna hinnay kalah caagid yoo baahah iyyah yan num wonna hinnay gaaroyse cokmí buxal malkit xayyoysam xiqah.

Lani exxak Nammaya

Baaluk caddo maadewee awkih ikoyta xiinisaanam wagittaama

191. Rakiibo

1) Gaddaa kee ikoyta wagitta caagiida baaluk caddo maadeweeh yan awki kaa quuka numut awlima

2) Gaddaa kee ikoyta wagitta tuxxiiqitte xiinisaanam kee lowsiisaanam le gambik kaa quuka num kaxxa cubbi abam faxximta.

192. Ikoytâ lowsis kee melleb fayramisso

1) Awka quuka num taama qembiseek lakal numma alsih addat sidiica sumaq elle tan aracal baaluk caddo maadeweeh yan awkih ikoyta lowsiisaah, melleb fayramisso yayyaaqe.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awka quukah yan num kaak esserah yan mago tenek ikoytâ lowsissoh maysaqarral uddurul heeweek magô mekla kaak raaqele.

193. Baaluk caddo maadewee awkak nagrâ gadda

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awki nagarah yan uddur awkah quuka num nagra hirgak

ከወላጆቹ አንደኛው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም አቃቢ ህግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ንኡስ ክፍል ሁለት

አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

191.መሰረቱ

1) **ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል ፡፡**

2) **ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡**

192.የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት

1) **ሞግዚቱ የሞግዚትነት ስራውን ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሶስት ምስክሮች ባሉበት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል የዋጋም ግምት ያወጣል፡፡**

2) **ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው እዳ ሲኖር በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካሰፈረው በስተቀር የእዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል፡፡**

193.አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት

1) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሶስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል የዋጋውንም ግምት ያወጣል ፡፡**

2) **ሞግዚቱ ከውርስ ሀብት ውስጥ ድርሻ ያለው**

naharat sidiica sumaq elle tan aracal nagarah ikoytah loowo abaah, melleb fayramisso yayyaaqe.

2) Awka quukah yan num nagrâ gaddih addat maglab yeellek ta ikoytâ loowoh maysaqarral aktubewaa kaa tekkek kay maglab kaak raaqele.

3) Ikoytâ loowo wonna hinnay fayramisso gitah akkewaytek wonna hinnay taamiteweenimih yaafeh yan taqabih awka quukah yan num kah esserimah.

194. Awka quukah yan numih ikoyta baaluk caddo maadewee awkih ikoytat elle tangale gurra

1) Awka quukah yan num baaluk caddo maadewee awkih ikoyta kay ikoyta lih kaak angalewaytuh faxxiima cubbi abam faxximta.

2) Baxsa luk baaluk caddo maadeweeh yan awkih maalu wonna hinnay ikoyta quukah yan num sinni bankih kontil wonna hinnay isi migaaqal daffeysam wonna hinnay haam kaah maxiqqimta.

195. Maali sanadittee kee kalah gaalih tan duyye/masruf elle daffeyta caalat wagittaama

Baaluk caddo maadewee awkih ikoyta lowsiisaanam wagittaamal taqabi bahtam akkewaytek maali sanaditteey, gaalih tan duyyeey, faxximta kubebaa kee kalah tah celtah tan tuma inkih awka quukah yan num bayaanamak, finqitaanamak elle bayewaan gurral meqe aracal haam faxximta.

196. Cokmí buxah qaaqa

እንደሆነ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል ።

3) **የንብረት ቆጠራው ወይም ግምቱ በአግባቡ ባለመከናወኑ ወይም ባለመሰራቱ ለሚደርሰው ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅበታል ።**

194.የሞግዚቱ ንብረት አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ

1) **ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ከግል ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት።**
2) **በተለይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገንዘብ ወይም ንብረት ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂሳብ ወይም በራሱ ስም ማስቀመጥ ወይም ማድረግ አይፈቀድለትም ።**

195.የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ውድ እቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር የገንዘብ ሰነዶችን ውድ እቃዎችን ጠቃሚ ጽሁፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፉ ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ ማስቀመጥ አለበት።

196.የፍርድ ቤት ስልጣን

1) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ የልጁ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ**

1) Baaluk caddo maadewee awka quuka num xaltani akkewaytah tan uddur ta awkih gaddaay, meqe xiinisso wagittaamal quukah yan numuh miracsenta yacayuh awkak iroh loowan xaltani wonna hinnay baaluk caddo maaddeh tan toobokoo kee maqanxiixik numuk teeni cokmí buxal essero xayyoysam xiqah.

2) Cokmí buxa baaluk caddo maadeweeh yan awkih gadda amolladih caalatal quuka numih xiqtoo kee awki tuxxiq qeedaalisak ikoytâ xiinisso wagittaamal meqem akak tableh tan miracsenta tacee.

197. Baaluk caddo maadewee awki acwah wonna hinnay nagrah kaat tabta ikoyta wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awki acwa wonna hinnay nagarah ikoyta tabsah yan num ikoytâ xiinisso wagittaamal meqeh kak iyyan gexsit miracsentitte quuka dagar akah kataannah amrisam xiqah.

2) Gexsit miracsentitte katayak taamitoonu xiqeweenik wonna hinnay baaluk caddo maadeweeh yan awkih tuxxiiqil taqbi kataysuwaam yublen ken tekkek quukeeni miracsentitte kaah akah massoysan innah cokmí buxa esseram xiqah.

198. Kabxâ massoynaanii kee kalah tah celta massoynaani wagittaama

1) Kabxaay, sanaaqatta wonna hinnay kalah tah celta massoynaani baaluk caddo maadeweeh yan awkih gaddat edde yeneenik iroh loowan

ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

2) **ፍርድ ቤቱም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል ።**

197.አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት

1) **አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ንብረት የሚያሥተላልፍ ሰው የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሰራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል ።**

2) **የአሰራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመስራት የማይቻል ወይም አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ሞግዚቱ መመሪያዎቹ እንዲስተካከሉለት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል ።**

198.ስለንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

1) **የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ፣ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት**

xaltanik wonna hinnay baaluk caddo maaddeh tan toobokoo kee maqanxiixik numuk teeni xayyoysah yan essero inaa kee abba akkewaa quukeeni ikoyta lowsiisuh wonna hinnay elle tan innal bisoh hayuh cokmí buxa amrissam xiqtah.

2) Cokmi buxa ta amri yaceeh yan uddur awka quukaanam magide sugtuwaytamaay, quukaanamih xiqtoo kee baaluk caddo maadewee awkih tuxxiq hangit haanam faxximta.

199. Inkinki ikoyta kalaanam wagittaama

1) Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih ikoytah tan kaxxa duyeey, aksiyoon kee maali sanaditte kalan xiqah.

2) Awki abba wonna hinnay inal akkewaytek caagid yoo baahah iyya faxe num essero xayyoysah yan waqdi cokmí buxa kalaanamih miracsenta yacayuh wonna hinnay kalti abekaltah tanim kalalaanam xiqaanah.

200. Baaha numuh mekloonuh inta sanaditte wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkih abba wonna hinnay ina akkewayta quukeeni baaha numuh mekloonay inta sanaditte awki gadda tekke ayrook qembisak sidiica alsih addat akah kalan innah wonna hinnay awki migaaqal tunkuttubeh tan sanaditte akah milaagimtannah abam faxximta.

2) Awka quukah yan num essero kaal xayyowtah

ሊያዘው ይችላል ።

2) **ፍርድ ቤቱ ይህንን ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትነቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሞግዚቱን ችሎታና አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።**

199.አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ

1) **ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን አክስዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶችን ለመሸጥ ይችላል ።**
2) **በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጭ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል።**

200.ለአምጪው እንዲከፈል ስለሚሉ ሰነዶች

1) **አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለአምጪው እንዲከፈል የሚሉ ሰነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሰነዶች እንዲለወጡ ማድረግ አለበት ።**

2) **ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ግዴታ ነጻ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል**

201.እዳዎችና ገቢ ገንዘቦች

tan waqdi cokmí buxa ta maasayyak lani maasayyak (1) madqimte dirkik curri yakkuh amrissam xiqtah.

201. Magoogaa kee culentí lakqooqa

1) Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih magooga awki gaddak ankusuk/kalak mekla.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awkah mekkeltimtam faxxiima kappitaal kee culenta kaah hirga.

202. Kappitaal maksab le taamal asissaanam wagittaama

1) Maali caddibna 3000 birriik daga tekkek baaluk caddo maadewee awkih kappitaal, kaa quukah yan num maksab le taamal kaah asisam faxximta.

2) Cokmí buxa ta maasayyak lani maasayyak /1/ madqimte lakqoh caddibna taysiisem xiqtah.

203. Uddúr waado

1) Kappitaal awka quuka numih gaba edde culeh yan sidiica alsih addat maksab le taamal asisaanam faxximta.

2) Cokmí buxa uddur caddibna taysiisem xiqtah.

3) Cokmí buxa faxximtam tublek maksab le taamal asisewee maaluh kaa quukah yan num taqabi gidyat akah meklannah kaal tackumem xiqtah.

204. Culentitte

1) **ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ እዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል ።**

2) **አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል ስለመቀበሉ በማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጣል ።**

202.ካፒታልን አትራፊ በሆነ ስራ ላይ ስለማዋል

1) **የገንዘብ መጠን ከ3000 ብር በላይ የሆነ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ካፒታል፣ ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ስራ ላይ ማዋል አለበት ።**

2) **ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል።**

203.የጊዜ ገደብ

1) **ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሶስት ወራት ውስጥ በአትራፊ ስራ ላይ መዋል አለበት ።**

2) **ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል።**

3) **ፍርድ ቤት አሰፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአተራፊ ስራ ላይ ላላዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይችላል።**

204.ገቢዎች

1) **አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆን ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል ።**

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkih culentitte dudda allewaytah tan uddur gaddak kalak maynub kee barittoh ayfaafayal kaah akah asannah kaa quukah yan num qaaqisel yacee.

2) Cokmí buxa gersinnal madaqteh akkewaytek ta ayfaafayal assah tan lakqo ummaan alsal qaaqiseh mekla.

3) Meklah caalat qaaqisee kee quukah yan numih sittingeyil wonna hinnay cokmí buxa taceeh tan margaqa rakiibo abak yaysiiseenim xiqqimtah.

205. Mardeh ambalaalitte

Cokmí buxa idini akah teceem akkewaytek quuka num abah yan mardeh ambalaalitte awki baaluk caddo edde maadeh yan sidiica sanataak lakal abbinoysaanamih dirki kaal matan.

206. Nagra wagittaama

1) Awki nagrak geyah yan ikoyta quukah yan num kaah hirga.

2) Awka quukah yan num nagrâ gadda mago mekelu inkinnah xiqeweeh akkewaytek nagra mafaxa iyyam maxiqa.

207. Acwa wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkah yaceenih yanin acwa tu maxiqa iyyeh akkewaytek quukah yan num mahirga iyyam maxiqa.

2) Baritelleh yaceenih yanin dagoo acwak iroh awka quukah yan num baaluk caddo

2) ፍርድ ቤቱ በሌላ አካኋን ካልወሰነ በስተቀር ለዚህ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፈላል::

3) የአከፋፈሉ ሁኔታ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት ሊሻሻል ይችላል ።

205.የኪራይ ውሎች

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሶስት ዓመታት በኋላ እንዲፈጽማቸው አይገደድም።

206.ስለውርስ

1) ልጁ በውርስ የሚገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል።

2) ሞግዚቱ የውርስ ሀብት እዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም ።

207.ስለስጦታ

1) አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት አይችልም ።

2) በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጭ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም ።

208.የዋስትና ግዴታ መግባት የማይቻል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው

maadeweeh yan awkih ikoyta awki migaaqal acwah yaceem maxiqa.

208. Caabî dirkit culaanam xiqewaanam wagittaama

Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih ikoyta gersi numih magoh caabih yabbixsiisem maxiqa.

209. Kalkaala wagittaama

Sitta elle waanah yanin tuxxiq alfi birriik addah aneweek wonna hinnay baaluk caddo maadeweeh yan awkih tuxxiq wagittaamal cokmí buxa idnisewaytek awka quukah yan num caagid kalkaalal yaymurruqem maxiqa.

210. Awka quuka num baaluk caddo maadeweeh yan awka lih abah yan ambalaalitte wagittaama

1) Awka quukah yan num cokmí buxa kaah idnisseh akkewaytek baaluk caddo maadeweeh yan awkih ikoyta xaamam, mardeh edde xoqaysimam wonna hinnay kalah faxe qaynatih ambalal kaalluk abam maxiqa.

2) Tonnah kaa quukah yan num cokmí buxa kaah idnisseh akkewaytek baaluk caddo maadewee awkal faxe qaynatih gar wonna hinnay lakqo elle esseran gar hirgam maxiqa.

211. Abud wagittaama

Cokmí buxa kaah idnisseh akkewaytek awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih migaaqal anud ambalal abam maxiqa.

212. Baaluk caddo maadewee awka lih

እዳ በዋስትና ሊያሲዝ አይችልም።

209.ስለ ግልግል

ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከአንድ ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም።

210.ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች

1) **ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈጸም አይችልም።**
2) **እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውንም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም ።**

211.ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም።

212.አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ

1) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እድሜ ከ14 ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የልጁ እድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ**

agaaradaanam faxximtam wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awki karmak 14 addah yeneh akkewaytek kaa quukah yan num awki karma kaah idnissa caddibnaa kee kaa wagsissah tan fayya le caagiida ugutta uddur baaluk caddo maadeweeh yan awka mabbaloysam faxximta.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awkah idini yaceenim kaa quuka num essertimiyyak macatta.

213. Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awki taamituh kaah yacee idini wagittaama

1) Baaluk caddo maadewee awkih karmaa kee maali duddak ugut abak ummaan ayroh caagid wagitta ambalaalitte dubuk akah abannah quuka num idini yaceem xiqah.

2) Ta idini annaak yaceem yantacawwem xiqah.

3) Abina abbinoysoonuh cokmí buxah idini faxxiimek faxe gital ayroh addah caagidi iyyaanam maxiqqimta.

4) Baaluk caddo maadeweeh yan awki 1000 birriik dagah dirkit kaa culussam tekkek ta abni ayroh addah caagidi kak iyyaanam maxiqqimta.

214. Quuka numul yaalluwaa xalu wagittaama

Baaluk caddo maadeweeh yan awki quuka numih idinil edde cula dirkitte quuka num sidochaytô dagarih caabi yaanama.

215. Farrimtu

ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት ።።

2) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም ።።**

213. ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሰራ ስለሚሰጠው ፈቃድ

1) **አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ እድሜና የገንዘብ አቅም መሰረት በማድረግ የእለት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል ።።**

2) **ይኸው ፈቃድ በዝምታም ሊሰጥ ይችላል ።።**

3) **ድርጊቱ እንዲፈጸም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የዕለት ጉዳይ ሊባል አይችልም ።።**

4) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከ 1000 ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የእለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም ።።**

214. በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ነው።።

215. ኑዛዜ

1) **ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደሰው ልጅ ስም ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም።።**

2) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 አመት ሳይሞላው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም።።**

1) Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih migaaqal farrimtu abam maxiqa.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awki 16 sanat kibe kalah farrimtu abam maxiqa.

3) Baaluk caddo maadeweeh yan awki 16 sanat kibe kalah abah yan farrimti 16 sanat kibek sarra duugumewaamah xalu mayaalla.

216. Ikoyta lowsiisuh awka quuka num aba awqenta wagittaama

Awka quukah yan num baaluk caddo maadewee awkih tuxxiiqih isik yayyaaqeh yan awqentitte kaah akah gacsaanamih gar le.

217. Gabbaaqu xayyoysaanam wagittaama

1) Awka quukah yan num baaluk caddo maadeweeh yan awkih gaddih xiinissoh caalat kee cisab wagittaamal gabbaaqu massoysak yabbixem faxximta.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awkak iroh loowimta xaltani wonna hinnay baaluk caddo maaddeh tan toobokoo kee maqanxix sitta lih wonna hinnay rike rikeh essero xayyoysan waqdi awka quukah yan num xiinissoo kee cisab gabbaaqih akah yablen innah aba.

218. Abbinoosu

Ta madqak maasayyak 186 ilaa 188 tan madqooqi awka quukaanamah edde abbinowta yaanama.

Fereyhaytoh Exxa

Baaluk caddo maadeweeh yan awka dacrisoonuh tan edde xintittet tatraanam katassah tan xalu

3) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ 16 ዓመት ሳይሞላው የሚደረገው ኑዛዜ 16 ዓመት ከሞላው በኋላ ባይሰርዘውም ውጤት አይኖረውም ።

216.ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደረገው ወጭ

ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው ።

217.ሪፖርት ስለማቅረብ

1) ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሳቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት ።

2) አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንዶሞች እህቶች በጋራ ወይም በተናጠም ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሳብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል ።

218.ተፈጻሚነት

በዚህ ህግ ከአንቀጽ 186 እስከ 188 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ።

ክፍል አራት

አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት

ንኡስ ክፍል አንድ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስራዎች

219.መሠረቱ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከስልጣኑ በላይ

Laní exxak Iniki

Baaluk caddo maadewee awkih taamoomi

219. Rakiibo

Baaluk caddo maadewee awki kay qaaqak iroha bah yan gaanuun abtoota inkih oggol mali.

220. Baysaanam esseraanam wagittaama

Baaluk caddo maadeweeh yan awki abeh yan madqa rakiibo abtah tan abtoota akah baytannah essertam xiqtam baaluk caddo maadeh yan awka wonna hinnay nagre mara wonna hinnay awlaytiiti.

221. Ambalal aba marih bagí qidi

1) Ta madqak maasayyak 220 madqimtem taniimih gersi ambalal aba dagar awka lih ambalal akah culen tah abu axcuk idini le axcuk qado baguh aamantil yekke kaa tekkek ambalal sarrimaane le.

2) Gersi ambalal awki aaxigewaayat xoqqaysimak ta maasayyak lani maasayyak /1/ madqimtem mabbinowta.

222. Taduure lakqo wagittaama

1) Baaluk caddo maadewee awkah mekkeltime maali yadaarem xiqam ambalal yaggaraqquh malkit edde xayyoowe ayro maadeh sugeh caddibna dubuk akkele.

2) Ta caalatak iroh baaluk caddo maadeweeh yan awki gacsaamih dirki kaal matan.

223. Ambalaalak iroh takke qaaqaa kee gita maliinoh gadditaanama

Baaluk caddo maadewee awki gita maliinoh tan taamat faxxiime sinni gurral baxaaxitek wonna

የሚፈጽማቸው ህጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ ይሆናሉ ።

220.እንዲፈርስ ስለመጠየቅ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የፈጸማቸው ህጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም ወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ ናቸው ።

221.ስለተዋዋዩ ቅን ልቦና

1) **በዚህ ህግ አንቀጽ 220 የተደነገገው ቢኖርም ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲያደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል ።**
2) **ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት የተጠቀመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ተፈጻሚነት አይኖረውም ።**

222.ስለሚመለስ ገንዘብ

1) **አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጁ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል።**
2) **ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደደም።**

223.ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሀላፊነት እና ያለአግባብ ስለመበልጸግ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ህገወጥ በሆኑ ስራዎች ያለአግባብ የበለጸገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሀብሔር ውስጥ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ሀላፊነት እና ያለአግባብ ስለመበልጸግ በተደነገገው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

224.አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለው ስለማለት

hinnay gersi maral taqabi kataasa kaa tekkek meqem bar madqah addal ambalaalak iroh takke qaaqaa kee gita maliinoh baxaaxitaanamal madqimte madqa rakiibo abak akah essertimele.

224. Baaluk caddo maadekkah maadeh iyyaanam wagittaama

1) Baaluk caddo maadewee awki gufe kalah gufeh iyyeh yaabamah tah iyyaamah dubuk baaluk caddo maadeweemih sabbatah edde xoqoysimah yan gar mawaa.
2) Tonnah baaluk caddo maadeh iyyaamah ambalaalak iroh tekke qaaqa bahta taqabih kaal maloowimta.

Lani exxak nammaya

Quuka numuk gaanuun abtoota

225. Madab gexsitil tekke abtoota

1) Awka quuka num baaluk caddo maadewee awki abeh yan gaanuun abtoota inkih awki baaluk caddo gufe uddur abeemik loowimak qaaqah essertima.
2) Awka quuka num qaaqah essertimeyyo iyyaanamih dirkih edde culek wonna hinnay madqak ugutak dirki kaal anewayta kaa tekkek baaluk caddo gufewee awkih sabbatah abe gaanuun abtootah qaaqise miyakka.

226. Madqimte madqat tatraanam wagittaama

Madqimte madqat taturak awka quukah yan num abah yan abtootah awlaytiino le num kaah yeceen qaaqak iroh taamitah yan yan uddur gitah tanih tan awlaytiinô madqah baxxaqsitte abbinoowele.

227. Sidochaytô dagara

1) Cokmí buxa awka quuka numuh yeceen

1) **አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ሳይደርስ ደርሻለው ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያጣም።**
2) **እንዲሁም አካለመጠን ድርሻለው በማለቱ ከውል ውጭ የሆነ ሀላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም።**

ንኡስ ክፍል ሁለት

የሞግዚቱ ህጋዊ ድርጊቶች

225.በመደበኛ አኳኋን ስለተፈጸሙ ድርጊቶች

1) **ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የፈጸማቸው ህጋዊ ድርጊቶች ሁሉ፣ ልጁ አካለመጠን በደረሰ ጊዜ እንደፈጸማቸው ተቆጥሮ በሀላፊነት ያስጠይቁታል።**
2) **ሞግዚቱ በንላፊነት እጠየቅበታለው ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በህግ መሰረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈጸማቸው ህጋዊ ድርጊቶች ሀላፊ አይሆንም።**

226.የህግ ድንጋጌዎችን ስለመተላለፍ

የህግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ስልጣን በላይ በሚሰራበት ጊዜ አግባብነት ያለቸው የውክልና ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

227.ስለሶስተኛ ወገኖች

1) **ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሶስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ ፣ በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።**
2) **አካለመጠን ላልድረሰ ልጅ ንብረቱን የሰጠ፣ የተናዘዘ**

miracsenta sidochaytô dagar aaxigeweek wonna hinnay yaaxigeenim faxxiimewaytek quukah yan num miracsentat taturaanamaay, sidochaytô dagaral cina yaallem maxiqa.

2) Baaluk caddo maadeweeh yan awkah ikoyta yeceeh, kaah farriime wonna hinnay kaah cabe num quukiini miracsenta yacee waqdi ta maasayyak lani maasayyak 1 madqimtem abbinoowele.

228. Aftô/Milaagí quukeena wagittaama

Ta lani exxal tanih tan madqooqi duma suge quukeenih aftok yemeete numul edde abbinoowele.

Lani exxak sidocu

Qaaqal sinam essersissam xiqta abtoota

229. Quuka num wagittaama

1) Quuka num abah yan ikoytâ xiinissoh coocih sabbatah wonna hinnay miracsenti assakaxxewaayak wonna hinnay kay nafqi baaluk caddo maadewee awkih tuxxiq lih boodak abe abtoh baaluk caddo maadewee awka maadah yan taqabih inkih qaaqah essertimah.

2) Ta maasayyak lani maasayyak 1 tanih madqa milaagi quukeenal edde abbinowta.

Konoyhaytoh Exxa

Baaluk caddo maadewee awki duddi sinnah raaqam wagittaama

230. Duddi sinnak kaak elle raqtah tan sababitte wagittaama

Baaluk caddo maadewee awki dudda mali yaanam kaak raqtam

1) Baaluk caddo maadah yan waqdi

ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል።

228.ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንኡስ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ንኡስ ክፍል ሶስት

በሀላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

229.ስለሞግዚት

1) **ሞግዚቱ በፈጸመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለማክበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈጸሙ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በሀላፊነት ይጠየቃል።**

2) **በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።**

ክፍል አምስት

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

230.ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው፡-

1) **አካለመጠን ሲደርስ፤**

2) **ከአሳዳሪ እና የሞግዚት አስተዳደር ነጻ ይውጣ ሲባል ነው።**

2) Qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawqay iyyan saaku

Lani exxak iniki

Qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawqem wagittaama

231. Rihimi

Baaluk caddo maadewee awki ta madqak maasayyak 6 lani maasayyak 2 tanih tanim rakiibo abak rihim abe kaa tekkek rihim sabbatah qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawqe.

232. Baxsa le gurral qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawqeenim wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awki 14 sanat kibah yan waqdi qaaqise wonna hinnay quukeeni wonna hinnay ta caagid yoo baahah iyyah yan gersi num qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawquh cokmí buxa esseram xiqah.

2) Cokmí buxah essero xayyowtah tan waqdi awkí caalat kee qaaqisee kee quukeeni xiinissok currik yayyaaquh essereh yan sabab wagitak qaaqisee kee quukeeni xiinissok curri yakkem awkah meqem tublek essero hirigak idinisam xiqqimtah.

233. Xalu

Qaaqisee kee quukeeni xiinissok currih yawqe awki madqal baaluk caddo maademik loowima.

234. Katewaytam kinnim wagittaama

1) Baaluk caddo maadewee awki qaaqisee

ንዑስ ክፍል አንድ

ከአሳዳሪ እና የሞግዚት አስተዳደር ነጻ ስለመውጣት

231.ጋብቻ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ህግ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው መሰረት ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ ይወጣል።

232.በልዩ ሁኔታ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ ስለመውጣት

1) **አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ 14 አመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው፣ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲወጣ ለፍርድ ቤት መጠየቅ ይችላል።**

2) **ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ተመልክቶ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ መሆኑን ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል።**

233.ውጤት

ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣ ልጅ በህግ አካለመጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል።

234.የማይሻር ስለመሆኑ

1) **አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም።**

2) **በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም**

kee quukeenak curri yakkuh yeceen idnisso kalaanam maxiqan.

2) Rihim sabbatah geytimteh tan qaaqisee kee quukeeni xiinissok curri yakkeemih caalat rihim cabbitimaamah xali elle sugennal raaqa.

3) Ta maasayyak lani maasayyak 2 madqimtem taniimih rihim baati rihimih idnisen gaanuun karma daccarsimewayteemih sabab tekke kaa tekkek qaaqisee kee quukeení xiinissok curri yakkeenim wagittaamal cokmí buxa meqem akak tableh tan margaqa abtam xiqtah.

Lani exxak nammaya

Quukeeni taamah cisaabitte yaysixxigeenim wagittaama

235. Rakiibo

1) Quukeeni quukaanamih taamak gaba kala waqdi edde quukeena akkuk qaaqiseh yan num wonna hinnay nagara marah edde quukeh/xiiniseh yan cisab xayyoysam faxximta.

2) Tonnah quukeena akkuk xiiniseh yan num ikoyta inkih tabsaamaay, gar elle yan caalat kee kaa dirkissah tan magooga tenek yaysixxigem faxximta.

236. Ikoyta maysaqarral gacewaytam

1) Quukeeni quukaanamih taama leh yan uddur wonna hinnay baaluk caddo maadeweeh yan awkah nagrah yaceenih yanin uddur ikoytâ rorsitte maysaqarral haamak aylahite kaa tekkek awwki ikoyta nagrah wonna hinnay acwah geeh yan gadda faxe qaynatal

እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው ለጋብቻ የተፈቀደው ህጋዊ እድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከአሳዳሪ እና ሞግዚት አስተዳደር ነጻ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል።

ንዑስ ክፍል ሁለት

የሞግዚትነት ስራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ

235. መሰረቱ

1) ሞግዚቱ የሞግዚትነት ስራው ሲያበቃ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰው ወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሳብ ማቅረብ አለበት።

2) እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ ፣የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው እዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት።

236. የንብረቶች በመዝገብ አለመግባት

1) ሞግዚቱ የሞግዚትነት ስራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ የልጁን ንብረት በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይችላል።

2) ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

geysiisam xiqah.

2) Kalah tahak saduh yan alhum xayyooweh akkewaytek sumaq mari yaceeh yan qangara inki ikoyta baaluk caddo maadewee awkih ikoytak loowimta.

237. Cisaabitte faaticisaanam wagittaama

1) Quukeeni xiinissok currih yewqeh yan awki ta quukiini taamah cisaabitte faaticisa kaa tekkeeh karma kaak 18 sanat kibe kalah tenek cisab faaticiseek lakal ilaa inki sanat fanah faaticiseh sugeh yan cisab sinnih baysam xiqah.

2) Quukeeni xiinissok currih yewqeh yan awki cisab akah xayyoysannah quukeenah idini yeceeh sugem takkay immay tahak dagal tanih tan madqa abbinoowele.

3) Baaluk karma maadeweeh yan awki baaluk caddo maade mari kaa nagrah yan waqdi ta nagreenit awki quukeeni abeh yan cisab faaticiseenim wonna hinnay quukeena cisab xayyoysaamak currih yeyyeeqeenih yeneenik tahak dagal tan madqooqit yaabak moggodo abaanam maxiqan.

238. Yirga wagittaama

1) Baaluk caddo maadeweeh yan awkaay, awlaytit wonna hinnay nagre mari quukeeni taamah sabbatah quukeenal qaaqa wagsiisak xayyoysaanah yanin faxe malkit quukeeni taama edde cabe udduruuk qembissa haanam ilaa koona sanat fan xayyoose kalah sugen kaa

237. ሂሳቦችን ስለማጽደቅ

1) **ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣው ልጅ የሞግዚትነቱን ስራ ሂሳቦች ያጸደቀ እንደሆነና እድሜው 18 አመት ያልሞላው ከሆነ ሂሳቦቹን ካጸደቀ በኋላ እስከ አንድ አመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሳብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል።**

2) **ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ የወጣው ልጅ ሂሳብ እንዳያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።**

3) **አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አካለመጠን የደረሱ ሲወርሱት እንዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሳብ ያጸደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሳብ ከማቅረብ ነጻ አውጥተውት እንደሆነ፣ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም።**

238. ስለ ይርጋ

1) **አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ፣ወኪሎች ወይም ወራሾች በሞግዚትነት ስራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለሀላፊነት የሚያቀርቧቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት ስራውን ከተወበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳሉ።**

2) **ሆኖም አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም።**

tekkek yirgak ugutak waasimaanah.

2) Takkay immay baaluk caddo maadewee awki ikoyta kaah gacsaanamih esseroh malkit xayyoysaanamih gar ahak dagal yan uddur taturek sarra takkeemih waaso mali.

Sagaalhaytô Mafdaga

Baxaabaxsa le madqooqi

239. Tabaatabsí madqa

1) 1952 yewqeh yan meqem bar madqa

a/Sehda wagittaama iyyah yan kitaabakteeni addal maasayyak 198 ilaa 338

b/ Ramad kee nagra wagittaama iyyah yan nammehaytoh kitaabih addal maasayyak 550 ilaa 825 tanih tan madqooqi ta madqah addat tanih tan caagiidal abbinos miyaalla.

2) Ta madqa saddah tan madqaa kee baritellê gexsititte ta kuktih addat tan caagiidal abbinos miyaalla.

240. madqak ugutak geenih sugen garitte wagittaama

1) Ta madqa faaticimtak naharat sugteh tan gaanuun caaloota geysiisoonuh qusba madqa essertah tan miizaanissoosa dumak baxsa leemih dumî madqak ugutak geytimteh sugteh tan gaanuun caaloota elle sugtennal raaqele.

2) Ta madqa faaticimtak naharat dumaahî madqak ugutak geytimteh sugteh tan gaanuun caaloota geysisseh tan xalitte ta

ምዕራፍ ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

239.መሸጋገሪያ ድንጋጌ

1) በ 1952 በወጣው የፍታህብሄር ህግ ፤

ሀ/ ስለሰዎች ከሚለው አንደኛ መጽሀፍ ውስጥ ከአንቀጽ 198 እስከ 338፤

ለ/ ስለ ቤተዘመድ እና ስለውርስ ከሚለው ሁለተኛ መጽሀፍ ውስጥ ከአንቀጽ 550 እስከ 825 ያሉት ድንጋጌዎች በዚህ ህግ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

2) ይህን ህግ የሚቃረኑ ህጎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

240.በቀድሞ ህጎች መሰረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች

1) ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ህጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገንት አዲሱ ህግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን፣ በቀድሞው ህግ መሰረት ተገኝተው የነበሩት ህጋዊ ሁኔታዎች ጸንተው ይቀጥላሉ።

2) ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ህግ መሰረት ተገኝተው የነበሩት ህጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸውን ውጤቶች ይህ ህግ አይለውጣቸውም።

241.በእንጥልጥል ስላሉ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች

ይህ ህግ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ የቤተሰብ ጉዳይ

madqa makorissa.

241. Wanxexxelit tan buxâ marih caagiidah daqwat wagittaama

Ta madqa faaticimtak naharat qembimteh tan buxâ marih caagiidah daqwat edde qembimteh tan madqa rakiibo abak gaba kak kalelon.

242. Edde xintaa kee miracsenta yayyaaqeenimih qaaqa

Rakaakay xiinissô malah-buxa ta madqah abnissoh edde xinta wonna hinnay miracsenta tayyaaqem xiqtah.

ክርክሮች በተጀመሩበት ህግ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

242.ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ ህግ አፈጻጸም ደንብ ወይም መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡